ዋስትና ዲጅታል ዜና መጽሔት
ቅጽ 1 ቁጥር 2



# በመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር በኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዴስክ በየስድስት ወሩ የሚዘጋጅ

ሰኔ 2017
አዲስ አበባ

የአስተዳደሩ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች

# ተልዕኮ

የማህበራዊ ዋስትና ዐቅድ አመራርን በማዘመን የተገልጋዮችን እርካታ ማሳደግ

# ራዕይ

በ2022 ዓ.ም የጡረታ ባለመብቶችን ገቢ መካከለኛ ደረጃ ደርሶ ማየት

# ዕሴቶች

ተገልጋይ ተኮር!
አክብሮትና አብሮነት!
መደጋገፍና መተማመን!
ጥራትና ፍጥነት!

# መሪ ቃል

ለዋስትናዎ እንተጋለን!



8926

# የዋስትና ዲጅታል ዜና መጽሔት የውስጥ ይዘቶች

- ማኅበራዊ ዋስትና
- ዓበይት ክንውኖች
- ማኅበራዊ ተሳትፎ
- የማኅበራዊ ዋስትና ሕግ
- እንግዳ

tgedefa2022@gmail.com

## የአዘጋጆች መልዕክት

ሰላም ውድ አንባቢያን እንደምን ከረማችሁ። ዋስትና ዲጅታል ዜና መጽሔት የዝግጅት ክፍል በአስተዳደሩ የተከናወኑ ዋና ዋና ጉዳዮች በየስድስት ወሩ እያዘጋጀ ለአንባቢያን ያደርሳል። በቅጽ 1 ቁጥር 1/ 2017 በመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የተከናወኑ ዋና ዋና የማህበራዊ ተሳትፎ፣ የተካሄዱ የውይይት መድረኮች፣ የተከበሩ በዓላት፣ የተሰጡ ስልጠናዎች እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ ዜናዎችና ሌሎች ግንዛቤ የሚፈጥሩ ጽሑፍ ማቅረባችን ይታወሳል። አሁንም እንደተለመደው በቅጽ 1 ቁጥር 2 በ2017 በሁለተኛ ግማሽ ዓመት የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎች እና ሌሎች አስተማሪ የሆኑ ጉዳዮችን ይዛ ብቅ ብላለች።


ውድ አንባቢያን ለመጽሔታችን ይዘት መሻሻል የአንባቢያን አስተያየት እና ጥቆማ ወሳኝ በመሆኑ አስተያየታችሁን በነጻ ስልክ ቁጥር 8926 ወይም በኢሜይል tgedefa2022@gmail.com ብትልኩልን ምስጋናችን የላቀ ነዉ።

መልካም ንባብ!!

## መግቢያ

**የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ዋና ዓላማ የመፈፀም አቅም በማሳደግ የመንግስት አገልግሎት ጡረታ ዐቅድን ማጠናከርና ማስፋት፤ የኢንቨስትመንት ፈንዱን በማዳበር የጡረታ ባለመብቶችን ገቢ በየጊዜው ማሻሻል እና በፈንድ አስተዳደር የመልካም አስተዳደር ችግርን በመቅረፍ የፈንዱን ቀጣይነትና አስተማማኝነት ማረጋገጥ ነው። አስተዳደሩ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት እንዲችል የሚያከናውናቸውን ሥራዎች በኮሙኒኬሽን ሥራ ማገዝ እና ውጤታማ ማድረግ ተገቢ ነው።**

**በመሆኑም የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዴስክ የአስተዳደሩን ዓላማ በማሳካት ረገድ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። ዴስኩ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ትኩረት አድርገው ስሰራባቸው ከነበረው ጉዳዮች መካከል የውስጥ ኮሙኒኬሽን ውጤታማነትን የማሳደግ፣ የግንዛቤና የህዝብ ግንኙነት ሥራዎችን የማሳደግ፣ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለዜጎች የመረጃ ተደራሽነትን የማስፋት እና የአስተዳደሩን የማህበራዊ ተሳትፎን በሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ሽፋን እንዲያገኝ ነው። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ዋና መ/ቤትን ጨምሮ በአስሩም ሪጅን ጽ/ቤት በአጠቃላይ ለ3,206,279 ዜጎች በተለያዩ የመረጃ መስጫ ዜዴዎች መረጃ ተደራሽ ተደርጓል።**




**ይህ የተዘጋጀው ዋስትና ዲጅታል ዜና መጽሔት በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ የሚዘጋጅ ሲሆን ዜናዎቹ በአምስት ክፍሎች ተከፋፍለው የተዘጋጁ ናቸው።**

# ማኅበራዊ ዋስትና

## የማኅበራዊ ዋስትና የዕድገት ምዕራፎች

ቀደም ሲል በዚሁ የማህበራዊ ዋስትና ዲጂታል መጽሄት ቅጽ 1 ቁጥር 1 /2017 ዕትም ላይ ዓለም አቀፉ የስራ ድርጅት ማኅበራዊ ዋስትናን አስመልክቶ በ102/52 (ILO) ያወጣውን ድንጋጌ መነሻ አድርገን አለምአቀፋዊ ሁኔታዎችን እና የትኩረት ዘርፉን ለማየት ተሞክረዋል:: ይህ ድንጋጌ አሁንም ድረስ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ አለም አቀፋዊ ስምምነት ነው:: ለመሆኑ ከILO ድንጋጌ (1952 እ.ኤ.አ) በፊት የማህበራዊ ዋስትና ታሪክ ወይም የዕድገት ምዕራፎቹ ምን ይመስላል? በአጭሩ እንቃኘዋለን::

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የማህበራዊ ዋስትና ሦስት የዕድገት ምዕራፎችን አልፏል:: በ19ኛው ክፍለ ዘመን ተግባራዊ ይደረግ የነበረው የቢስማርክ አሠራር ወይም ማህበራዊ መድን ከማህበራዊ ዋስትና የዕድገት ምዕራፎች ውስጥ ቀዳሚው ነው:: የሠራተኛውን መዋጮ ብቻ መሠረት ያደረገ በመሆኑ የጡረታ አበሉም ዝቅተኛ ነበር:: በወቅቱ ለዚህ የማህበራዊ ዋስትና መጀመር ምክንያቶች ነበሩ በሚል የሚነሱ አንዳንድ ጉዳዮች አሉ:: ለአብነትም በ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት፣ በወቅቱ አገልግሎት ላይ ይውል የነበረው ቴክኖሎጂ ኋላ ቀር በመሆኑ በሠራተኞች ላይ በየጊዜው የሚያስከትለው ጉዳት እየተበራከተ መምጣት፣ ለሥራ ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ የሚፈልሰው ህዝብ መብዛት፣ በዚህም የተነሳ የሠራተኛው ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መምጣት፣ በዝቅተኛ ደመወዝ ሳቢያ ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ በመሆኑ የቁጠባ አለመኖር፣ ሠራተኛው በሚያጋጥሙት የተለያዩ እክሎች የተነሳ መደበኛ ስራውን ማከናወን ሲያቅተው ከስራ መፈናቀል፣ በዚህም ሳቢያ በሚከሰት የገቢ መቋረጥና በዕድሜ ምክንያት ስራ የሚለቁ ሰዎች መተዳደሪያ ማጣት የሚሉት በዋናነት የሚነሱ ነበሩ::

ሁለተኛው የማህበራዊ ዋስትና ምዕራፍ እ.ኤ.አ. ከ1930-1952 ድረስ የተሻሻለ የመድህን ዋስትና የታየበት የማህበራዊ ዋስትና ዘመን ተከታዩ የዕድገት ምዕራፍነ ው:: ይህ ዘመን ከመጀመሪያው በተሻለ መልኩ ከሁለቱም፣ ማለትም ከሠራተኛው እና ከአሠሪው የሚዋጣ መዋጮን መሠረት ያደረገ የጡረታ አበል ክፍያ የሚፈጸምበት ነበር:: አለም አቀፉ የስራ ድርጅትም ከተመሰረተበት እ.ኤ.አ ከ1919 ጀምሮ ሠራተኞችን የሚመለከቱ መብቶችን እና አነስተኛ የማህበራዊ ዋስትና መመዘኛ ደረጃዎችን ያረቀቀበት፣ ብሎም በአባል ሀገራት ተግባራዊ እንዲደረጉ ጫና ማሳደር የቻለበት በመሆኑ ለሠራተኛው የተሻለ የመድህን ዋስትና ታይቶበታል:: በወቅቱም ለጡረታ አበል አወሳሰን የግል መረጃን ብቻ መሰረት ማድረጉ ቀርቶ በጋራ ዐቅድ መመራት የተጀመረበት ነበር::

የማህበራዊ ዋስትና እንደ ሰብዓዊ መብት የታየበትና ብዙ ሀገሮችም በህገ መንግስታቸው ውስጥ ሽፋን እንዲያገኝ ያደረጉበት ሦስተኛው የዕድገት ምዕራፍ የማህበራዊ ደህንነት ዘመን በሚል ይታወቃል:: ማንኛውም ዜጋ ሠራተኛ መሆን ወይም መዋጮ መክፈል ሳይጠበቅበት በዜግነት ብቻ ሽፋኑን እንዲያገኝ የተደረገበት ሲሆን፣ ይህም

ማህበራዊ ዋስትናን ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ማድረግ የተጀመረበት ነው፡፡ ወጪውም በአጠቃላይ በመንግስት ገቢ እና ግብር /Tax/ ይሸፈናል፡፡

ከላይ በአጭሩ ለመዳሰስ በሞከርናቸው ሦስቱ የማህበራዊ ዋስትና የዕድገት ምዕራፎች ውስጥ ዜጎች የሽፋኑ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በመዋጮ እና ያለመዋጮ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ማህበራዊ ዋስትናን ለህብረተሰቡ ለማዳረስ ሀገራት የሚጠቀሙባቸውና በዓለም ላይም የተለመዱት አሠራሮች እነዚሁ ናቸው፡፡ መንግስታትም የሀገራቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አንዱን ወይም ሁለቱንም በመተግበር የዜጎቻቸውን ማህበራዊ ደህንነትና ጥቅሞች ያስጠብቃሉ፡፡ በመዋጮ ላይ የተመሰረቱት የማህበራዊ መድን፣ የጤና መድን፣ ፕሮቪደንት ፈንድ ሲሆኑ፣ በመዋጮ ላይ ያልተመሰረቱት ደግሞ ሁሉን አቀፍ፣ የአሰሪ ግዴታና ማህበራዊ ድጋፍ የሚሉት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ማህበራዊ ዋስትናን በቀዳሚነት የጀመሩት ጀርመን እና እንግሊዝ ናቸው፡፡ ጀርመን ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ፣ እንግሊዝ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጋር በተያያዘ በወቅቱ የገጠሟቸውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተለያዩ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞችን በመጠቀም በሂደት የፈቱ ሀገሮች ናቸው፡፡

በሀገራችን በስራ ላይ ያለው የማህበራዊ ዋስትና ዓይነት ማህበራዊ መድን የሚባለው ሲሆን፣ አሠራሩም ከአሠሪው እና ከሠራተኛው በሚዋጣው መዋጮ ላይ ይመሰረታል፡፡ በዚህ የዋስትና ዓይነት ሽፋን ያገኘ ሠራተኛ በሚከፍለው የጡረታ መዋጮ መብቱ ይረጋገጥለታል፡፡ አሠራሩም መድህን መርህ፣ የመብት ተንሸራሻሪነት መርህ፣ የሦስትዮሽ አመራር መርህ እና በግዴታ የመመስረት መርህ በሚሉት አራት መሠረታዊ መርሆዎች ይመራል፡፡

ማህበራዊ ዋስትና የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ብቻም ሳይሆን የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም አካል ተደርጎ በመቆጠሩ በአሁኑ ጊዜ የማህበራዊ ፍትህንና የዜጎችን እኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን ላልተዳረሰባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎችና ሠራተኞች ማዳረስ የሀገሮች አጀንዳ እየሆነ መጥቷል፡፡ በሀገራችንም ከመንግስት ክፍለ ኢኮኖሚ በተጨማሪ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተሰማርተው የሚገኙ ዜጎችም ሽፋኑን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

ምንጭ፡- በተቋሙ የተዘጋጁ የተለያዩ የስልጠና ሠነዶች

## ዓበይት ክንውኖች

### መድረክ

**አስተዳደሩ በግማሽ ዓመቱ የዕቅዱን 90 በመቶ ማከናወኑ ተገለጸ**

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የ2017 የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ መድረክ ከጥር 12-16/2017 ድረስ በአዳማ ከተማ አካሄደ፡፡



በዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ መድረኩ ላይ የአስተዳደሩ የ2017 የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለውይይት የቀረበ ሲሆን፣ በ6 ወራት ውስጥም የዕቅዱን 90 በመቶ አከናውኗል ተብሏል፡፡

በግምገማ መድረኩ ላይ እንደተገለጸው የመድረኩ ዓላማ የተሻሉ አሠራሮችን እና ልምዶችን በመውሰድ ሥራዎችን ማጠናከር በመሆኑ፣ በቀጣይ ጊዜ የተሰጡ አስተያየቶችን በማሻሻል የላቀ አፈጻጸም ይዞ መገኘት ይገባል ተብሏል፡፡

ሪጅን ጽ/ቤቶችም የተቋሙን ሪፎርም ለማስቀጠል ያላቸውን ዕውቀትና ዐቅም አሟጠው በመጠቀም በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት አሠጣጥ እንዲጠናከር ሁሉም ኃላፊነቱን መወጣት አለበት የተባለ ሲሆን፣ 8926 ነጻ የስልክ መስመርን ተገልጋዮች እንዲጠቀሙበት የማስተዋወቅ እና የማበረታታት ስራዎችም ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ተብሏል፡፡

በተጨማሪም የብሄራዊ ዲጂታል መታወቂያ ያላወጡ የጡረታ ባለመብቶችም በአቅራቢያቸው በሚገኙ የምዝገባ ማዕከላት በመገኘት እንዲመዘገቡና መታወቂያውን እንዲይዙ ማድረግም ይገባል ተብሏል፡፡







በተያያዘም በሁለተኛው ግማሽ ዓመት የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ላይ ጥር 22/2017 ከዋናው መስሪያ ቤት ሠራተኞች

ጋር ውይይት ተካሂዷል። ለውይይት በቀረበው ዕቅድ እንደተገለጸው በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት፣ የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣ የለውጥ ስራዎች ትግበራን ማጠናከር እንዲሁም የሕግ የበላይነት እና ተጠያቂነትን ማጎልበት ላይ ትኩረት ያደረጉ ስራዎች ይከናወናሉ ተብሏል።

## በመንግስት ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች ላይ ውይይት ተካሄደ

የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ሰራተኞች በመንግስት ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች ላይ የካቲት 13/2017 የአስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት ውይይት አካሄዱ።



በውይይት መድረኩ ሰፋ ያለ ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን በተለይ የሀገር ግንባታ/ Nation building/ ከማጠናከር፣ የኢኮኖሚ ልማትን ከማፋጠን፣ ማህበራዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጡ ሥራዎችን በውጤታማነት ከማስቀጠል፣ ውጤታማ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ከመስራት፣ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ውጤታማነትን ከማረጋገጥ፣ ጠንካራ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ሥራ ከመስራት፣ የጠንካራ ፓርቲ ግንባታን አጠናክሮ ከማስቀጠል፣ ብሔራዊነት ገዥ ትርክት ግንባታ ከማጠናከር፣ ውጤታማ የሰላም ግንባታ ሥራ ከመስራት እና የፍትህ ዘርፍ ውጤታማነትን ከማሳደግ አንጻር በትኩረት መስራት እንደሚገባ በዝርዝር ቀርቧል።



ተሳታፊዎችም በቀረበው ሰነድ ላይ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ያነሱ ሲሆን፣ የጉባኤውን ውሳኔዎች እና አቅጣጫዎች ህዝብን በሚጠቅም መልኩ እንዲተገበሩ ጥልቅ ግንዛቤና የጋራ ርብርብ በማድረግ የመንግስት ሰራተኞች የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንደሚገባቸው ተመላክቷል።

ሁለተኛው የብልፅግና ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ከጥር 23 - 25 ቀን 2017 በአዲስ አበባ ከተማ በዓድዋ ድል መታሰቢያ አዳራሽ መካሄዱ ይታወሳል።

## የመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር አመራሮች እና ሠራተኞች 'የመጋቢት 24 ፍሬዎችና ቀጣይ የሀገራችን ተስፋዎች" በሚል መሪ ሀሳብ ውይይት አደረጉ

የመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር አመራሮች እና ሠራተኞች "የመጋቢት 24 ፍሬዎችና ቀጣይ የሀገራችን ተስፋዎች" በሚል መሪ ሀሳብ መጋቢት 22/2017 ዓ/ም ውይይት አድርገዋል። ውይይቱን በንግግር የከፈቱት የአስተዳደሩ

ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዳባ ኦርያ ሲሆኑ እንደ እሳቸው ገለጻ የለውጡ መንግስት ከመጋቢት 24/2010 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ ውስብስብ ፈተናዎችን እየተጋፈጠ አኩሪና እምርታዊ ድሎች እያስመዘገበ ለህዝቡ ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ወደፊት እየሄደ ያለ መንግስት በመሆኑ የመጋቢት ፍሬዎችን ለሠራተኞች ግንዛቤ በመፍጠር የመጣውን ለውጥ ለማስቀጠል የታለማ መድረክ መሆኑ ገልጿል፡፡



እንደሳቸው ገለጻ በሀገራችን የቆየውን ውስብስብ ችግሮችን ግምት ውስጥ ያስገባ አሁን የሚንገኝበትን አለም አቀፋዊ ሁኔታን በመለየት ወደፊት የሚሄድ መንገድና አቅጣጫ የያዘ ስርዓት መሆኑን ሰራተኛው ጠንቅቆ በመረዳት የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበትም አንስቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለውይይት የሚሆን ሰነድ የቀረበ ሲሆን ቀኑ ብልፅግና ፓርቲ ስልጣን ላይ ከወጣ በኂላ በርካታ ተግባራት ተሰርተው ውጤትም አይተናል እንደ ሃገር የለውጡ የብልፅግና ፣ የሃገር በቀል እሳቤ መጀመሪያ በመሆኑ በልዩነት ልናስበው እና ልንተገብረው ይገባል ብለዋል፡፡



በመጨረሻም ለውጡን አጠናክሮ በማስፋትና ዘላቂነቱን በማረጋገጥ የዜጎችን ህይወት በሁለንተናዊ መልኩ ለመለወጥና የሀገራችንን እና የዜጎቻችን ህልምና ርዕይ ለማሳካት እኛ የአስተዳደሩ ሠራተኞች መልካም ስኬቶቻችንን እያስቀጠልን፣ ጉድለቶቻችንን እያረምን በላቀ ትጋትና ቁርጠኝነት ማስቀጠል እንዳለብን ተገልፆ መድረኩ ተጠናቋል ፡፡ በውይይት መድረኩ ላይ የመሃል ሪጅን ሃላፊዎች እና ሠራተኞች ተሳትፈዋል፡፡



**ትናንት፣ ዛሬና ነገን ለኢትዮጵያ ልዕልና!**

## የፓናል ውይይት ተካሄደ

የመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር የዋና መ/ቤት፣ የአዲስ አበባ እና የመሃል ሪጅን ጽ/ቤት አመራሮች እና ሠራተኞች መጋቢት 24ን ምክንያት በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ እና

መልካም አስተዳደር በሚል ሪዕስ መጋቢት 23/2017 ዓ.ም የፓናል ውይይት አካሂደዋል።



ፓናሊስቶቹ እንደገለጹት የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም መልካም አስተዳደር ለማስፈን በመጀመሪያ ጽንሰ ሃሳቦቹን በደንብ መረዳት እንደሚገባ ገልጸዋል።




በተለይ በአስተዳደሩ ሪፎርም ከተተገበረ ወዲህ ቀልጣፋ እና ሰው ተኮር አገልግሎት እየተሰጣ ያለ ቢሆንም አሁንም ቢሆን እያንዳንዱ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት እቅድ በማዘጋጀት ከዋና መ/ቤት እስከ ቅርንጫፍ እና መስክ ጽሕፈት ቤት እየተተገበረ መሆኑን ፓናሊስቶቹ አንስቷል።

አክለውም የዕቅዱን አፈጻጸም በተመለከተ ለወደፊት ተከታታይ ጥናታዊ መረጃ በማሰባሰብ ያልተስተካከሉ ችግሮች ካሉ እንዲስተካከሉ ይደረጋልም ብሏል።

የፓናሉ ተሳታፊዎችም የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ውይይት የተደረገበት ሲሆን በተለይ የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎችን በማጠናከር በሁሉም ሪጅን እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተገልጋዮችን እርካታ በተጨባጭ ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት ይገባል ብለዋል።



በፓናል ውይይቱ መዝጊያ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ የሰጡት የአስተዳደሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዳባ ኦርያ እንደገለጹት ባለፉት ዓመታት አስተዳደሩ በርካታ የህግ ማዕቀፎች በማሻሻል፣ የሰው ኃይል አቅም ግንባታ እና ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸው ቀጣይነት ያለው የመልካም አስተዳደርን ለማስፈን እና የሚጠበቀውን ውጤት ከማረጋገጥ አንጻር ከዋናው መ/ቤት እስከ ቅ/ጽ/ቤት በተደራጀው የኬዝ-ቲም እንቅስቃሴ የሚወሰን በመሆኑ ሁሉም ሠራተኞች በትኩረት መስራት እንደሚገባቸው ገልጸው የፓናል ውይይቱ ተጠናቋል።

## ማኅበራዊ ተሳትፎ

### ለአረጋዊያን የመኖሪያ ቤት ህንጻ ለመገንባት የግንባታ ማስጀመሪያ ስነስርዓት ተከናወነ

የመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር በባህር ዳር ከተማ ለ14 የአቅም ውስንነት ላለባቸው አረጋዊያን አባወራዎች የሚሆን መኖሪያ ቤት ለመገንባት ግንቦት 22/2017 ዓ.ም የአስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች፣ ሠራተኞች እና በባህር ዳር ከተማ የጣና ክ/ከተማ አስተዳደር ተወካዮች በተገኙበት የግንባታ ማስጀመሪያ ስነስርዓት ተከናወነ።

የሚገነባውን የህንጻ ዲዛይን የሰራው ዱኒያ አማካሪ መሐንዲሶች ሲሆን፣ ግንባታዉን ለማካሄድ ደግሞ ጥላሁን አበበ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ቃል መግባቱን በስነ ስርዓቱ ላይ ተገልጿል።

አስተዳደሩ ከዚህ በፊትም የአቅም ውስንነት ላለባቸው ዜጎች የመኖሪያ ቤቶችን እድሳት ያከናወነ ሲሆን፣ በሲዳማ ክልል በይርጋለም ከተማም ከ10 ሚሊየን ብር በላይ በሚገመት ወጪ ለ8 የአቅም ውስንነት ላለባቸው የጡረታ ባለመብቶችና ግለሰቦች መኖሪያ ቤት በማስገንባት ማስረከቡ ይታወሳል።



### የሌማት ትሩፋት ፕሮጀክት ለመተግበር የመሰረት ድንጋይ ተቀመጠ

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዳባ ኦርያ በሸገር ከተማ ኮዬ ፈጬ ክ/ከተማ በቱሉ ዲምቱ ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚተገበር የሌማት ትሩፋት ፕሮጀክት የማስጀመሪያ ሥነስርዓት ላይ በመገኘት ሰኔ 13/2017 ዓ.ም የሸገር ከተማ ከፍተኛ አመራሮች፣



የኮዬ ፈጨ ክ/ከተማ አመራሮች፣ አጋር አካላቶች እና የአስተዳደሩ ከፍተኛ፣ መካከለኛ አመራሮችና ሠራተኞች እንዲሁም የትምህርት ቤቱ አመራሮችና መምህራኖች በተገኙበት የመሰረት ድንጋይ አኖሩ።




ይህ የሌማት ትሩፋት ፕሮጀክት ከ8-10

የተሻለ ዝርያ ያላቸዉ የወተት ላሞች እና ከ500 በላይ የሚሆን የእንቁላል ጣይ ቄብ ዶሮዎች የማርባትን ስራ መነሻ በማድረግ የሚጀመር ሲሆን ዓላማውም የተማሪዎችን ምገባ ለማገዝ መሆኑን ተነግረዋል።

ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ፋይናንስን በሚመለከት የእንስሳት እና የእንስሳትና መኖ ግዥ እንዲሁም ሌሎች ፕሮጀክቱን ለመጀመር የሚያስፈልገው ወጪ አቢስንያ ባንክ፣ ዳሸን ባንክ፣ ኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ፣ ሕብረት ባንክ፣ ኦሮሚያ ባንክ እና አባይ ባንክ እንደሚሸፍኑ እና የግንባታ ሥራዎችን በሚመለከት አሴፍ ኢንጂነሪንግ ሙሉ በሙሉ በራሱ ወጪ እንደሚገነቡ በስነ-ስርዓቱ ላይ ቃል ገብተዋል።

ፕሮጀክቱን ሙሉ ለሙሉ ለመተግበር ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ ይፈጃል ተብሎ ይገመታል።

## የ2018 በጀት ዓመት የአረንጓዴ አሻራ ማስጀመሪያ መረሃ ግብር ተከናወነ

የመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር የ2018 በጀት ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በሸገር ከተማ ኮዬ ፈጬ ክ/ከተማ በቱሉ ዲምቱ ቁጥር 2 የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቅጥር ግቢ ሰኔ 13/2017 ዓ.ም የማስጀመሪያ መረሃ ግብር ያከናወኑ ሲሆን ከ500 በላይ የሚሆኑ ለምግብነት የሚያገለግሉ እንደ አቡካዶ፣ ማንጎ፣ ፓፓዬ እና ሌሎች ችግኞችን ተክለዋል።



አስተዳደሩ ለበርካታ ተከታታይ ዓመታት የአረንጓዴ አሻራ ሥራዎችን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን በዘንድሮ ዓመት "በመትከል ማንሰራራት" በሚል መሪ ሀሳብ ዋና መ/ቤትን እና የሪጅን ጽ/ቤት ሰራተኞችን በማስተባበር ከቀድሞ በበለጠ ለመትከልና ለማንከባከብ መዘጋጀታቸውን በመረሃ ግብሩ ተመላክተዋል።



# የአቅም ግንባታ ስልጠና

### ለአስተዳደሩ ሠራተኞች በቪዲዮ ኮንፈረንስ ስልጠና ተሰጠ

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር በሁሉም ሪጅን እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ለሚገኙ ሠራተኞች ታህሳስ 22 እና 23 ቀን 2017 በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በቪዲዮ ኮንፈረንስ ስልጠና ሰጠ።

ለሁለት ቀናት በቆየው በዚህ ስልጠና በጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 959/2015፣ ስለጡረታ አበል አወሳሰን፣ በማስረጃ አደረጃጀት፣ በስነ-ምግባር መመሪያ፣ በስራ ላይ ስነ-ምግባር እና በተቋማዊ ተግባቦትና ገጽታ ግንባታ ላይ ትኩረት ያደረጉ ርዕሰ ጉዳዮች የተነሱ ሲሆን፣ ስልጠናውም ሠራተኛው በስራ ላይ ሊኖረው የሚገባውን ስነ-ምግባር በማስገንዘብና የመፈጸም አቅሙን በማሳደግ ለተቋማዊ ገጽታ ግንባታ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ በማድረግ የተቋሙን አገልግሎት አሠጣጥ ቀልጣፋ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው::

በስልጠናው የዋናው መስሪያ ቤት፣ የሁሉም ሪጅን እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የተካፈሉ ሲሆን፣ ለሁለት ቀናት በቪዲዮ ኮንፈረንስ በተካሄደው ስልጠና ወንድ 906፣ ሴት 819 በአጠቃላይ 1725 የአስተዳደሩ ሠራተኞች ተካፍለዋል::

## የተከበሩ በዓላት

### 49ኛው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በደማቅ ሁኔታ ተከበረ

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳዳር በሃገር አቀፍ ደረጃ ለ49ኛ ጊዜ "ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሁሉን አቀፍ ለውጥ በሴቶች ተሳትፎ ይረጋገጣል" በሚል መሪ ሃሳብ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን /ማርች 8/ በዓል የካቲት 28/2017 ዓ.ም የተለያየ ሁነቶችን በማከናወን በድምቀት አከበሩ::

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና




አስተዳደር ኦፐሬሽን ዘርፍ ም/ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጥላሁን በቀለ በበዓሉ መክፈቻ ላይ እንዳሉት፣ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1908 በኒውዮርክ ግዛት ከስራ ሰዓት እና ከክፍያ መሻሻል እንዲሁም ከምርጫ አሳታፊነት ጋር በተያያዘ ይታይ የነበረው ኢ-ፍትሃዊነት እንዲቀረፍ ለመጠየቅ ሴቶች ተቃውሞ በማስነሳታቸው ምክንያት የሴቶች ቀን አከባበር የተጀመረ መሆኑን ታሪክ የሚናገር መሆኑን ጠቅሰው ዕለቱም ሴቶች በማህበረሰቡ የሚደርስባቸውን ጭቆና ተቋቁመው በፖለቲካውና በምጣኔ ሃብቱ



ያስመዘገቡት ውጤት የሚዘከርበት እና የሴቶችን ዕኩልነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ስራዎች የሚሰሩበት ነው ብለዋል::



ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንዳሉት የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደርም የተቋቋመበትን ተልዕኮ ለማሳካት የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ በማሳደግ ረገድ በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ የሚገኝ መሆኑን እና በተቋሙ የተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሴቶች በአመራርነት እንዲመደቡ በማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ጥረት የተደረገ ቢሆንም፣ በሚፈለገው ልክ በቂ ባለመሆኑ አስተዳደሩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በዕለቱም የበዓሉን አከባበር አስመልክቶ የተዘጋጀ ሰነድ ለውይይት የቀረበ ሲሆን፣ ሁላችንም በቤታችንም ሆነ በስራ ቦታችን በሁሉም መስክ የሴቶችን ተሳትፎ ማጠናከርና በሀገር ዕድገት ላይ ያበረከቱትን ጉልህ አስተዋጽኦ በማንሳት ማበረታታት እንደሚጠበቅ ተነስቷል፡፡ በሀገራችንም ሆነ በዓለማችን በሚታዩ ግጭቶች ላይ በዋናነት ሴቶች ለችግር ሲዳረጉ ታዝበናል፣ በመሆኑም የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማሳደግ ሰላም ቅድሚያ የሚሰጠው ነውና ይህን ማረጋገጥ የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን ሊዘነጋ አይገባም ተብሏል፡፡

በበዓሉ አከባበር ላይ የአስተዳደሩ ከፍተኛ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የተገኙ ሲሆን፣ በሁሉም ሪጅን ጽ/ቤቶችም የተለያዩ ሁነቶችን በማከናወን ተከብሯል፡፡

## የማኅበራዊ ዋስትና ሕግ

### መመሪያ ቁጥር 1038/2017 ምን ያህል ያውቃሉ?

የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ከአሠሪና ከሠራተኛ የጡረታ መዋጮ ይሰበስባል፡ የጡረታ ፈንዱንም ያስተዳድራል፡፡ የጡረታ ፈንድ ማለት በማህበራዊ መድን ዐቅድ ከአሰሪውና ከሠራተኛው የሚሰበሰብ መዋጮ እና ለክፍያ የሚውል በአንድ ቋት የተጠራቀመ ገንዘብ ነው፡፡ ከጡረታ ፈንዱ ወጪ የሚደረገው ገንዘብ ለጡረታ ክፍያ፣ ለኢንቨስትመንት እና ለአስተዳደሩ አስተዳደራዊ አገልግሎት ብቻ ይውላል፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ አሠሪ መ/ቤቶች የሚፈለግባቸውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለአስተዳደሩ ገቢ ባለማድረግ በጡረታ ፈንዱ ላይ ጫና ሲፈጥሩ ቆይተዋል፡፡ ይህን ለመከላከልም በአዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ በነበረው ድንጋጌ የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ በወቅቱ ገቢ ሳያደርግ የቆየ የመንግስት መሥሪያ ቤት በባንክ ካለው ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ የማስደረግ ስልጣን እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌም ውዝፍ የጡረታ መዋጮን በሚፈለገው ልክ ገቢ ማስደረግ አላስቻለም፡፡

ይህም የጡረታ ፈንዱን ዘላቂነት የሚጎዳ በመሆኑ ከአሰሪ ተቋማት ሊሰበሰብ ያልቻለ ውዝፍ የጡረታ መዋጮን በመሰብሰብ ወደ ጡረታ ፈንዱ ገቢ እንዲደረግ በተሻሻለው

አዋጅ ቁጥር 1267/2014 አንቀጽ 12(12) ላይ አስተዳደሩ መመሪያ እንዲያወጣ፣ በሚያወጣው መመሪያ መሠረትም የመንግስት መ/ቤቱን ንብረት በመሸጥ ገቢ እንዲያስደርግ ኃላፊነት ተጥሎበታል፤ ስልጣንም ተሰጥቶታል።

አስተዳደሩም በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የጡረታ መዋጮን የመ/ቤቱን ሀብት በመያዝና በመሸጥ ገቢ ማስደረግ የሚያስችለውን መመሪያ ቁጥር 1038/2017 አውጥቷል።

በመሆኑም በዚህ ጽሁፍ በመመሪያው ውስጥ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች መካከል ሀብትን ስለማስከበር፣ ስለማይከበሩና ስለማይያዙ ሀብቶች፣ እንዲሁም ሀብት ስለመያዝ የተወሰኑ ነጥቦችን እናነሳለን።

## 1. ሀብትን ስለ ማስከበር

ሀብትን ስለ ማስከበር ስንል በመመሪያ ቁጥር 1038/2017 በተገለጸው መሠረት ውዝፍ/ያልተከፈለ የጡረታ መዋጮ ያለበትን አሠሪ መ/ቤት ሀብት ወይም ንብረት ከመያዙ በፊት ባለበት እንዲቆይና እንዳይንቀሳቀስ ለማድረግ አስተዳደሩ የሚወስደው እርምጃ ነው። ይህም በፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ሊወጣባቸው ከማይችሉት በስተቀር በአሠሪ መ/ቤቱ የተያዘ ቤት ወይም ህንጻ፣ በኩባንያ ውስጥ ያለው የአክሲዮን ድርሻ እና ሌሎችም ሊሸጡ የሚችሉ ሀብቶችን ያጠቃልላል።

በመመሪያው እንደተገለጸው የአሠሪ መ/ቤቱ ሃብት የሚከበረው የሚፈለግበትን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ሳይከፍል ሲቀርና በአካውንቱ ላይ በቂ ገንዘብ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ነው።

አስተዳደሩ በአዋጅ ቁጥር 1267/2014 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ባወጣው በዚህ መመሪያ ያልተከፈለ/ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ዕዳ ያለበትን አሠሪ መ/ቤት የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ሃብቱን በመያዝና በግልጽ ጨረታ በመሸጥ የሚገኘውን ገቢ ወደ ጡረታ ፈንድ ያስገባል።

በመሆኑም በተለይም በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ከአላስፈላጊ ውጣ ውረድ ለመዳን የሚፈለግባቸውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## 2. ስለ ማይከበሩና ስለ ማይያዙ ሀብቶች

አስተዳደሩ ያልተከፈለ/ውዝፍ የጡረታ መዋጮውን ለመሰብሰብ የባለዕዳውን መ/ቤት ሃብትና ንብረት በመያዝና በመሸጥ የጡረታ መዋጮውን ገቢ ማስደረግ እንደሚችል ግልጽ ቢሆንም፣ እንደ መ/ቤቶቹ ልዩ ባህሪና አግባብ እንዲሁም ለአጠቃላዩ ህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶች የማይያዙና የማይከበሩ ይሆናል። ይህም መ/ቤቱ ለተቋቋመበት አላማ ማስፈጸሚያ የሚሆኑና አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴውን የማያስተጓጉሉ ሀብትና ንብረቶችን ይጨምራል።

### 3. ሀብት ስለመያዝ

ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ያለበት የመንግስት አሠሪ መ/ቤት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ያለበትን ዕዳ ሊከፍል ወይም ለመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ቀርቦ የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይገባል:: ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ግን ባለ ዕዳ መ/ቤቱ ካለበት ዕዳ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ሃብቱ ወይም ንብረቱ እንዲያዝበት ይደረጋል::

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ ከሠራተኛው እና ከአሠሪ መ/ቤቱ በየወሩ እየተቆረጠ ለጡረታ ፈንድ ገቢ መሆን ያለበትን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ለመሰብሰብ እንዲቻል ነው::

የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ ፈንድ በአሠሪውና በሠራተኛው መዋጮ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን የፈንዱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ይገባል::

## የጡረታ መታወቂያ ማሳደስ ለምን አስፈለገ?

የጡረታ መታወቂያ በአመት አንድ ጊዜ የአስተዳደሩ ሪጅን እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚያወጡት ፕሮግራም መሠረት ይካሄዳል::

በጡረታ መታወቂያ ዕደሳት ወቅት በአካል ተገኝቶ ማሳደስ የእያንዳንዱ የጡረታ ባለመብት ኃላፊነት ነው::

የጡረታ መታወቂያ ዕደሳት ማካሄድ አስፈላጊ ከሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ በዋናነት ምን ያህል የጡረታ ባለመብቶች እንዳሉ ለማወቅ፣ የክፍያውን ገንዘብ በመታወቂያ እድሳት ውጤት መሠረት ለመላክ እና ሕጉ ከሚፈቅድላቸው ውጪ ያላግባብ የሚከፈል ክፍያን በመከላከል የጡረታ ፈንዱን ለመጠበቅ ነው::

የጡረታ ፈንዱን መጠበቅ ደግሞ የሁሉም ኃላፊነት በመሆኑ የጠረታ ባለመብቶች ያላግባብ የሚከፈል ክፍያን በማጋለጥ የበኩላቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል::

## 8926 ነጻ ስልክ

### በ8926 ከተገልጋዮች ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች

**የተገልጋይ ጥያቄ:- በራስ ፈቃድ ጡረታ ለመውጣት አገልግሎትና ዕድሜ ስንት መሆን አለበት?**

8926 ምላሽ:- በመንግስት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 1267/2014 አንቀጽ 19(3) መሠረት ቢያንስ 25 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሠራተኛ (የዲሲፕሊን ችግር ከሌለበት) የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ 5 ዓመት ሲቀረው ጀምሮ የጡረታ መብቱን መጠየቅ ይችላል::

**የተገልጋይ ጥያቄ:- መ/ቤታችሁ የሚሰጠውን አገልግሎት ብትነግሩኝ?**

8926 ምላሽ፡- የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞችን የማህበራዊ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚሰራ ተቋም ሲሆን፣ በአዋጅ ከተሰጡት ዋና ዋና ተግባራት መካከልም በሥራ ላይ ያሉ የመንግስት ሠራተኞች መመዝገብና የጡረታ መለያ ቁጥር መስጠት፣ የጡረታ መዋጮ ገቢ መሰብሰብ፣ የጡረታ አበል መወሰንና ክፍያ መፈፀም ይጠቀሳሉ፡፡

**የተገልጋይ ጥያቄ፡- ብሔራዊ መታወቂያ ከጡረታ ጋር ምን አገናኘው?**

8926 ምላሽ፡- በአዋጅ ቁጥር 1267/2014 አንቀጽ 5(1) ላይ እንደተመለከተው የብሔራዊ መለያ ቁጥር የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል በደነገገው መሠረት ነው የጡረታ ባለመብቶች እንዲመዘገቡ የተደረገው፡፡ በተጨማሪም የብሄራዊ መታወቂያው ከባንኮች እና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር አንድ ወጥ እና ሁሉን አቀፍ አሠራር ለመዘርጋት ስለሚያግዝ ነው፡፡

**የተገልጋይ ጥያቄ፡- የጡረታ መለያ ቁጥር የለኝም፣ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?**

8926 ምላሽ፡- የሠራተኛን የጡረታ መለያ ቁጥር መጠየቅ ያለበት አሠሪ መ/ቤቱ ነው፣ የሠራተኛው መ/ቤት የጡረታ መለያ ቁጥር ያልተሰጠው ከሆነ የህይወት ታሪክ፣ የቅጥር ደብዳቤ፣ ፎቶ ግራፍ እና በቅፅ ጡ.1 ፎርም በመሙላት ለሠራተኛው የጡረታ መለያ ቁጥር መጠየቅ ይቻላል፡፡

**የተገልጋይ ጥያቄ፡- የኑሮ ውድነቱን መቋቋም አልቻልንም፣ የጡረታ አበል አይጨመርም ወይ?**

8926 ምላሽ፡- በመንግስት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ 1267/2014 በግልጽ እንደተመለከተው የጡረታ ባለመብቶች በየጊዜው የሚከሰተውን የገበያ ዋጋ ለውጥና የኑሮ ውድነት በተወሰነ ደረጃ መቋቋም እንዲችሉ በአስተዳደሩ ሥራ አመራር ቦርድ የፈንዱን የመክፈል አቅም እየታየ እንዲሁም ከግል ድርጅቶች ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር እና ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመነጋገር የጡረታ አበል ማስተካከያ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ እንዲደረግ ያዛል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቱ ማስተካከያ የሚያደርግ ከሆነ ያሳውቃል፡፡

## መዝናኛ

### የሁለት ሽማግሌዎች ወግ

ሁለት የተወሰነ የእድሜ ልዩነት ያላቸው ሽማግሌዎች ስላሳለፉት የቀደሞ ህይዎታቸው እየተጫወቱ ሳለ በእድሜ አነስ የሚለው ሽማግሌ ጥቂት ለሚበልጠው ሽማግሌ ጥያቄ ያቀርብለታል፡፡ በህይወት ዘመንህ ተመኝተህው የተሳካልህ ነገር አለ? ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ በእድሜ ከፍ ያለው ሽማግሌም ሲመልስ አዎ አለ፡፡ በልጂነቴ ጥፋት አጥፍቸ እናቴ ጸጉሬን ስትይዘኝ በጣም ስለሚያመኝ ምነው መላጣ በሆንኩ እል ነበር ይሄው አሁን ተሳክቶልኛል አለ ይባላል፡፡

# እንግዳ

የመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓትን በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ እና የሥርዓቱ ተጠናክሮ መቀጠል ለማኅበራዊ ፍትሕ፣ ለኢንዱስትሪ ሰላም፣ ለድህነት ቅነሳ፣ ለምርታማነትና ለልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው፤ በሥራ ላይ ያለውን የመንግሥት አገልግሎት የጡረታ ዐቅድ አቅም በፈቀደ መጠን በማጠናከር፣ አዋጆቹን በማሻሻል ለሥራው አፈጻጸም ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ጠልቀት ያለው ሪፎርም እያካሄደ ይገኛል፡፡ ከዚህ ሪፎርም ጋር በተያያዘ አቶ አሰፋ ማናዬ በአስተዳደሩ የዋና ሥራ አስፈጻሚ የፖሊሲና የማኅበራዊ ዋስትና ጉዳዮች አማካሪ የሆኑት በቅርቡ ስለሪፎርሙ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተው ነበር፡፡ ስለሆነም ሁሉም አካላት በደንብ እንድረዳው ስለተፈለገ በድጋሚ እንድታተም ተደርጓል፡፡ መልካም ንባብ!

**ማህበራዊ ዋስትና፡-** ግብዣችንን አክብረው ለዚህ ቃለመጠይቅ ፍቃደኛ ስለሆኑ ከልብ እያመሰገንኩ ከአንባቢያን ጋር እንድንተዋወቅ በመጀመሪያ ስምዎትን እና የሥራ ድርሻዎትን ቢነግሩን?

**እንግዳ፡-** ስሜ አሰፋ ማናዬ እባላለው፡፡ የስራ ድርሻዬ በመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር የዋና ሥራ አስፈጻሚ የፖሊሲና የማኅበራዊ ዋስትና ጉዳዮች አማካሪ ነኝ፡፡

**ማህበራዊ ዋስትና፡-** አስተዳደሩ ወደ ሪፎርም ሲገባ በዋናነት ትኩረት ያደረገባቸው ጉዳዮች ምን ምን ነበሩ?

**አቶ አሰፋ፡-** አስተዳደሩ ወደ ሪፎርም ሲገባ በዋናነት ትኩረት ያደረገው የጡረታ ዐቅድ ሥርዓትና አመራር ምሶሶዎች (pillars) ተብለው በሚታወቁ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ምሰሶዎች እንደየአገራት ተጨባጭ ሁኔታ የሚለያዩ ቢሆንም የዐቅድ አስተዳደር (Governance)፣ የፈንድ ዘላቂነት (Sustainability)፣ ፍትሐዊነት (Equitability)፣ የመክፈል አቅም ተመጣጣኝነት (Adequacy)፣ የተቋም የማስፈጸም አቅም (Institutional capacity limitation) በመነሻ ሀሳብነት የሚወሰዱ አንኳር ሪፎርም ጉዳዮች ናቸው፡፡ አስተዳደሩም እነዚህ መነሻዎች ይዞ ከ2011 ዓ/ም ጀምሮ ወደ ሪፎርም ገብቷል፡፡



**ማህበራዊ ዋስትና፡-** በሪፎርሙ የተመዘገቡ አንኳር ውጤቶች ምንድናቸው? ቢጠቅሱልን?

**አቶ አሰፋ፡-** አስተዳደሩ ለተራዘመ ጊዜ የሪፎርም ጥናት ሲያካሂድ ቆይቶ ከ2014

ዓ/ም ጀምሮ አዲስ የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ በማውጣትና በመተግበር ሪፎርሙን አሃዱ ብሎ ጀምሯል፡፡ አዲስ ማቋቋሚያ ደንብ በማጸደቅ አስተዳደሩ በአዲስ መልክ እንዲቋቋምና ከተልዕኮ አፈጻጸም አንጻር አግባባ ባለው መንግስታዊ አካል ሥር እንዲደራጅ ብሎም የሥራ አመራር ቦርድ የመወሰን አቅም ከፍ እንዲል እና እንዲሰፋ ተደርጓል፡፡ የሰው ሃይል ሥምሪቱን በአዲስ መዋቅር እንዲደራጅ እንዲሁም የተሻለ የክፍያ ሥርዓት እንዲኖር አድርጓል፡፡ የጡረታ ፈንዱ በተመረጡና አዋጭነታቸው በተረጋገጡ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ በመሰማራት ክፍያውን ከኢንቨስትመንት በሚገኝ ገቢ ብቻ መሸፈን እንዲችል የጡረታ ፈንድ ኢንቨስትመንት ስትራቴጂ አጸድቆ ወደሥራ ገብቷል፡፡ በተያያዘም የመክፈል አቅሙ እየተሻሻለ በመምጣቱ በአዋጁ መሠረት የጡረታ ባለመብቶችን ገቢ ለማሻሻል በየዓመቱ የአበል ማስተካካያ እያደረገ ይገኛል፡፡



አዋጁ የማስፈጸም አቅምን ያሳደገ በመሆኑ የጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሰብ እንዲሻሻል አስችሏል፡፡ ከሁሉ በላይ አስተዳደሩ የሚሰጠው አገልግሎት ‘ሰው ተኮር’ እንዲሆን የሠው ሃይሉን የአመለካከትና የሥነ-ምግባር ለውጥ ለማምጣት በስልጠናዎች፣ በመስክ ክትትልና ድጋፍ፣ በኬዝ ቲም አደረጃጀት እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ዕቅድ በመቅረጽ እየሠራ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የአገልግሎት አሰጣጡ በመረጃ ቴክኖሎጂ በተሟላ ሁኔታ አለመደገፉ ተጨማሪ ስራ የሚፈልግ ነው፡፡

**ማህበራዊ ዋስትና፡-** በሪፎርም ትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች ምን ነበሩ? ችግሮቹ እንዴት ተፈቱ?

**አቶ አሰፋ፡-** በሪፎርም ትግበራ ወቅት ካጋጠሙ ችግሮች መካከል ሠራተኞችና አመራሮች የሪፎርሙን አላማና ግብ በተሟላ ሁኔታ እንዲሁም በተመጣጠነ ደረጃ አለመረዳት መታየቱ፤ የጡረታ መዋጮ ገቢ የሚሰበስቡ አንዳንድ አካላት አሚጠው ወደ ጡረታ ፈንዱ ቋት ለማስገባት ወደ ኋላ ማለታቸው፤ ለጡረታ ባለመብቶች የአበል ማስተካከያ እየተደረገ ቢሆንም የኑሮ ውድነቱ እየበላው መሆኑ፤ አሰራሮችን በመረጃ ቴክኖሎጂ ለማስደገፍ የሚደረገው ጥረት በተለያዩ እክሎች ምክንያት በተሟላ አግባብ መተግበር አለመቻሉ የሚጠቀሱ ውስንነቶች ናቸው፡፡

**ማህበራዊ ዋስትና፡-** አስተዳደሩ ሪፎርሙን ከመተግበሩ በፊት ምን ደረጃ ላይ ነበር? አሁንስ ምን ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ይቻላል? ወይም መሻሻል የታየባቸው ጉዳዮች ምንድናቸው?

**አቶ አሰፋ፡-** አስተዳደሩ ሪፎርም ከመተግበሩ በፊት መነቃቃትና ተነሳሽነት የጎደለው የሰው ሃይል፣ የአገልግሎት ቅልጣፍና ውጤታማነት ማነስ፣ በጣም ደካማ የኢንቨስትመንት ሁኔታና የጡረታ መዋጮ ገቢ አሰባሰብ፣ አነስተኛ የጡረታ አበል እና የክፍያ ተደራሽነት ውስንነት የሚታይበት ነበረ፡፡ በአንጻሩ ከሪፎርም በኋላ የአስተዳደሩ ሥራ አመራር ቦርድ ውሳኔ ሰጪነት ከፍ ማለቱ፣ የጡረታ አበል ማስተካከያ በየአመቱ በማድረግ የጡረታ ባለመብቶችን ገቢ መሻሻሉ፣ የክፍያ ወጪዎችን ከኢንቨስትመንት በሚገኝ ገቢ መሸፈን መቻሉ፣ የአሰራር ማሻሻያዎች በመደረጋቸው ቅሬታ እየቀነሰ ከ0.5% በታች መውረዱ፣ የሰው ሃብት የሥራ ተነሳሽነት እያደገ መሆኑ በጥቂቱ የሚጠቀሱ መሻሻል የታየባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

**ማህበራዊ ዋስትና፡-** ከሪፎርም ትግበራ ጋር በተያያዘ የአስተዳደሩ ቀጣይ ዕቅድ ምንድነው?

**አቶ አሰፋ፡-** በቀጣይ የአስተዳደሩን የአሰራር፣ የቁጥጥር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በመረጃ ቴክኖሎጂ ማስደገፍ፣ ተቋማዊ መዋቅሩ የወቅቱን ቴክኖሎጂ በሚመጥን ደረጃ ማሻሻልና መተግበር እንዲሁም የኢንቨስትመንት መስኮችን በማስፋት ትርፋማነት ማሳደግ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

**ማህበራዊ ዋስትና፡-** በመጨረሻም ሊያስተላልፉ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ ቢገልጹ?

**አቶ አሰፋ፡-** አስተዳደሩ ሪፎርሙን በመተግበር መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና አገልግሎት አሰጣጡን ሰው-ተኮር ለማድረግ ጥረቶችን እያደረገ ነው፡፡ በዚህ ጥረት ውስጥ የአስተዳደሩ ሠራተኞች ዋንኛ ተዋናዮች ስለሆኑ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በየደረጃው ያሉ አመራሮችም ተልዕኳቸውን በአግባቡ ተረድተው ለስኬቱ መስራት አለባቸው፡፡



**ማህበራዊ ዋስትና፡-** የተጣበበ ጊዜዎትን መስዋዕት አድርገው ለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ አሰፋ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

# የካሜራ ዓይን


issa
issa
Joachim BREUER
ISSA President


ISSA
iood Practice
Award
www.issa.int
Prix AISS des
s pratiques
.int




Forum
curité sociale
IQUE

# የመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር

ዓላማችን የመፈፀም አቅም በማሳደግ የመንግስት አገልግሎት ጡረታ ዐቅድን ማጠናከርና ማስፋት፤ የኢንቨስትመንት ፈንዱን በማዳበር የጡረታ ባለመብቶችን ገቢ በየጊዜው ማሻሻል እና በፈንድ አስተዳደር የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመቅረፍ የፈንዱን ቀጣይነትና አስተማማኝነት ማረጋገጥ ነው፡፡



ነጻ ስልክ ቁጥር 8926